# የወያኔ ፅናትና የ እኛ ተክለ ሰውነት

ከዘመድ አገኘው

September 2, 2009

ለሰባዊ መብት በሚቆረቆሩና ስባዊ መብትን በሚረግጡ መሀል ያለው ፍልሚያ በሺሕ የሚቆጠሩ ንፁሀን በየእስር ቤቱ እንድታጎሩ ስያደርግ የዛኑ ያህል ደግሞ ክቡር ህይወት እንዲያልፍ ምክንያት ሆኖ በግፍ ይሚሰቃየውና ሐገሩን ጥሎ የሚሰደደውን ደግሞ ቤት ይቁጠረው።

ታዲያ በሰሜን አሜሪካን ውስጥ በእውነትና ሐሰት፣ በብዙው የኢትዮጵያ ሕዝብና በጥቂት የወያኔ መሪዎች መሐከል በአጠቃላዩ ለሰባዊ መብት በቆመውና ሰባዊ መብትን በሚጨፈልቀው መሐል ያለውን ወሳኝ የሆነ አመራርና አደረጃጀት፣እንዲሁም በተግባር የሚገለፅ የውሳኔ አተረጓገም፣ ስናወዳደር የጥቂቶቹ የወያኔ መሪዎች የመግዛት ፍላጎት ፅናት በቀላሉ የሚታይ ስላልሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመከራ ዘመን ገና የጀመረ ነው የሚያስመስለው። (ነገር ግን ለውጥ የሚያመጡት በሐገር ቤት ያሉት እንጂ በውጪ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የድረ ገፅ አዘጋጆች ወይም የሪድዮን ፕሮግራም መሪዎች ባለመሆናቸው ስጋታችን ይቀንሳል።)

የፖለቲካውን መዘውር ጨብጦ የሐገሪቷን ኢኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳይ እንዳሻው የሚያሽከረክረው የፖለቲካ ፓርቲ አጀንዳውንና ጥቅሙን ሊያስከብርበት የመረጠውና የሚገለገልበት መሳሪያ ጉልበት ነው።

በሌላ አባባል ስልጣኑን ጨብጦ በኢኮኖሚም የበላይ ሆኖ የፖለቲካ አጀንዳውን እየፈጸመ ለመዝለቅ በተግባር ከሚታይ የፈረጠመ ጉልበት ሌላ ምንም አማራጭ እንደሌለው በማመኑ የወሰዳቸው አረመኔያዊ እርምጃዎች አረጋግጠውልናል።

ፍትህ፣ እኩልነትና፣ ዲሞክራሲ፡፡ አንባ ገነናዊ ስልጣኑን የሚጋፉ ዋና ዋና ጠላቶቹ ናቸው። የሰባዊ መብትን ለማክበር እንኳን ቢፈልግ፣ ከመረጠው የስልጣን መወጣጫ መሳሪያ ጋር በፍጹም ስለማይጣጣም፣ ለእንደዚህ አይነት የአንባ ገነን አገዛዝ፣ የሰባዊ መብት ጥያቄ ማለት ይቅርታ የማይደረግለት አደገኛ የስልጣን ተቀናቃኝ ማለት ነው።

ዘር የማጥፋት እርምጃ የፖለቲካው አጀንዳው ባይሆን እንኳን፣ የስልጣን መንበሩን ሊጠብቅበት የመረጠው መሳሪያ ጉልበት ስለሆነ የሚያምፅ ጎሳ፣ የሚያድም ማህበረ ሰብ፣ የሚያስተባብር ሐይማኖት፣ አንድነት የፈጠረ ቡድን፣ በጅምላ መጨፍጭፍ ለትግራይ ነፃ አውጪ ወያኔ የመጀመሪያም የመጨረሻም ምርጫ ብቻ ሳይሆን በስልጣን ፉክክር ጨዋታ ምንም አይነት ሰው ሰራሽም ይሁን የተፈጥሮ ህግ
ቦታ እንደሌለው ያረጋገጠበት የጨዋታ ሜዳ ነው።

እነኚህ ከላይ ጠቀስ ጠቀስ የተደረጉት የወያኔ ባህሪዎች የተገመቱ ወይንም በፖለቲካ ትንታኔ የታሰቡ ሳይሆኑ በግብር የታዩ በመረጃ የተደገፉ የትላንትና ስራዎቻቸው የዛሪ ድርጊቶቻቸው የነገም እቅዳቸው እንድሆነ በማያወላዳ መልኩ በሚገባም ተገንዝበን እንድንፈራ ሆን ተብሎ በድርጊት እለት በለት የምናየውና የሚተላለፍልን መለክትም ነው።

በተጨማሪ ደግሞ ሊፈጠር ከሚችል የተፎካካሪ ጉልበት ሁሉ በልጠው ለመገኘት  በገንዘብ፣ በመሳሪያና፣ በቅጥር ነፍሰ ገዳዮች ብዛትና ጥራት፣ ጡንቻቸውን  ከማጎልበት ባሻገር ተፎካካሪያቸውን እውነተኛ ተፎካካሪ ሆኖ ከመምጣቱ በፊት የሚያውጁት ጦርነት የሚያረጋግጠው ከመግዛት ያነሰ የሚደራደሩበት ምንም አይነት አማራጭ እንደሌለ ነው። ለዚህ አባባል በግልፅና በድብቅ የሚገደሉት፣ በየእስር ቤቱ የታጎሩትና፣ በየግዜው የሚያወጡት የሰብአዊ መብትን የሚረግጡበት የህግ አይነቶች በቂ ማስረጃ ናቸው።

በተቃራኒው ደግሞ የሐገሩን ጉዳይ ጉዳዬ ነው በማለት ለሰላም ለብልፅግና ለዲሞክርሲያዊ ስራት መፈጠር ከሐገር ውጭ ደፋ ቀና የሚለው የሰሜን አሜሪካን  ሐገር ወዳድና በሪድዮን ጣቢያ የሚያገለግሉ፣ በድህረ ገፅ መረጃ የሚያቀብሉ፣ ለረጅም አመታት ሰልፍ በማዘጋጀት ብዙ የደከሙ፣ ወገኖች ድካማቸውን የሚጋራ ሐሳባቸውን የሚደግፍ ቡድን ብቅ ብሎ መቶ ሺ እናሰልፍ ቢል ትልቅ ማሰብ ወይንም በዙ ማሰብ እንደ ጥፋት ተቆጥሮ የዜና ሽፋንም ሆነ የማስታወቂያና የቅስቀሳ ድጋፍ በዘዴ ተነፈገ።

“ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከንባው ላይ ቂጢጥ” እንዲሉ እንዲያውም አንድ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ ጭራሽኑን እከሌን አጅብ ነው የምትሉኝ በማለት የሚልዮን ህዝብ ሰቆቃና በደል ከሳቸው ተክለ ሰውነት እንደማይበልጥ መናገራቸውን አንድ የሪድዮን ጣቢያ አዘጋጅ አጋልጠዋል።

ከላይ የተጠቀሰውን ቁርጠኛ የወያኔን አካሄድ ተመልክተን፣ በተክለ ሰውንት ውቃቢ ተኮፍሰን፣ ለባለቤትነትና ገንዘብ ለማሰባሰብ፣ ጉልበታችንን ስናለፋ፣ የኛ ያልሆነ ሐሳብ ዋጋ የለውም ብሎ በመዘርጠጥ ደባ መስራት ማስተዛዘብ ብቻ ሳይሆን የታሰርንበትን ገመድ ያጠብቀዋል፣ ደግነቱ የታሰርንበትን ገመድ የሚበጥስልን እዛው ሐገር ቤት ያለው በሰላምም ይሁን በሀይል ግብ ግብ የተያያዘው ግፍ አንገፈገኝ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።

በውጭ የሚደረገው እንቅስቃሴ የውስጡን እንዴት ያግዛል ሳይሆን፣ ባገር ቤት ጋዜጦች ጀግንነታችን እንዲወራ ከሆነ ውር ውር ይምንለው የከንቱነት ምልክት ነው፣ እዚህ የተያያዝነው ግብ ግብ የስርአት ለውጥ በሀገር ቤት እንዲመጣ ለማበረታታት መሆኑ ቀርቶ የመለስ ዜናዊ ኤርትራዊ መሆን የፈጠረብን ጥላቻ ብቻ የሚገፋን ከሆነ የውስጡን ትግል እንዳናግዝ እንቅፋት ነው የምንሆነው።

የስቱዲዮ ድምፅ ማጉያ ጨብጠን ለውጥ የራበውን ስደተኛ እያስጨበጨብን የገንዘብ ማሰባሰብ ፊታውራሪነት ከሆነ ታጋይ የሚያደርገን፣ በማንኛውም አይንት ክፍያ ወያኔን ከጫዋታው ውጭ ከማድረግ ውጭ ሌላ እኛም አማራጭ የለንም የሚል መልክት ሳይሆን የምናስተላልፈው፣ እዩኝ እዩኝ አይንት ጥፋት ነው የምንሰራው ማለት ነው።

ለማጠቃለል ያህል  ለሰባዊ መብት መከበርና በየግዜው በሐገርችን ውስጥ የሚደረገውን ጭፍጨፋ ለማስቆም በሐገር ቤት ውስጥ የሚደረገውን ትግል የአሜሪካን መንግስት የውጭ ፖሊሲ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እንዳያጨናግፍ እንዲያውም በግልባጩ ከኢትዮጵያ ሕዝብ

ጎን በማያወላዳ መልክ እንዲቆም የሚጠይቅ ሰላማዊ ስልፍ ላይ መተባበር፣ ማስተባበር፣ በግንባር ቀደምነት መምራት፣ መቀስቀስ፣ በሐገርችን ሕዝብ ላይ የሚፈፀመውን ግፍና ስቃይ መጋራት እንጅ ከእንትና ተክለ ሰውነት ማነስ ወይንም ከእንትን ድርጅት የበታች መሆን አይደለም።

ለረዥም ግዜ በተለያየ ሚዲያ ለስብአዊ መብት በአንድነት እንድንቆም የተጠራውን የህዝብ ጥሪ ልባቸሁ ዘልቆ ያልገባ የሰባዊ መብት ተቆርቋሪዎችና የፖለቲካ ስልጣን ጠያቂዎች!

እንግዲህ የፖለቲካም የድረ ገፅም የሬድዮንና የጋዜጣ አዘጋጆችና መሪዎች ይህ ስላማዊ ሰልፍ እስከዛሬ የደከማችሁበትን የተሰደዳችሁበትንና ብዙ መከራ የከፈልችሁበትን አላማ የሚያግዝ ስለሆነ እንደ ከዚህ በፊቱ ያላችሁን የህዝብ ፍቅር አሳዩበት።

ወያኔ ገዢ ከመሆን ሌላ ምንም ምርጫ እንደሌለው እንዳረጋገጠልን ሁሉ፣ እኛም ወያኔን ከመጣል ሌላ ምንም አማርጭ እንደሌለን አምነን የሐገር ቤቱን ትግል በሙሉ ለብ እንደምናግዝ እናረጋግጥና እጅ ለጅ ትያይዘን እንድንወጣ ያላችሁን አቅም በሙሉ በዚህ ጉዳይ ላይ አረባርቡት።

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይታደጋታል!!

ይህንን ፅሁፍ አስመለክቶ ለፀህፊው የሚሉት ካለ
ethiopiansmarchforfreedom@yahoo.ca